# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ልሳነ ህግ ጋዜጣ

ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19ኛ ዓመት አዋጅ ቁጥር 80
አሶሳ 2001 ዓ/ም


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 80/2001 ዓ/ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

መግቢያ

የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዲችል ያአባላቱን ቁጥር ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ኢንዲሁም ከዚህ በፊት የወረዳ ፍ/ቤቶች ውክልና ስላልነበራቸውና በአባልነት መወከላቸው አስፈላጊ መሆኑ፣ በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 (3)(1) መሠረት የሚከተለ ታውጇል፡፡

## 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የዳኞች አስተዳደር ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 38/1994 አንቀጽ 4ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር (ሐ)ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2 ማሻሻያ

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 38/1994 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) እንደሚከተለው ተሻሽሎዋል፡፡

1. በክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የሚወክሉ አራት የምክር ቤት አባላት-----አባል፡፡
2. በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር እንደሚከተለው አዲስ ንዑስ ፊደል (ረ) ተጨምሯዋል፡፡

(ረ) ከወረዳ ፍ/ቤቶች የሚመረጥ አንድ ዳኛ -----አባል ፡፡

## 3 አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ የልሳነ-ህግ ጋዘጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ ሚያዝያ 13ቀን2001ዓ/ም

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕረዚዳንት